- ***የተቋሙ ስልጣንና ተግባራት***

*የክልሉ መንግስት ም/ቤት የተቋሙን ስልጣንና ተግባራት እንደገና ለመወሰን ባወጣው በአዋጅ ቁጥር 89/ 2002 ዓ.ም አንቀጽ 6 መሰረት ለስራ አመራር ተቋም የተሰጡት ስልጣንና ተግባርና ኃላፊነቶች የሚከተሉት ናቸው ።*

1. *በየደረጃው የሚገኙ የክልላዊ መንግስቱ አካላት የሥራ አመራር ብቃት እንዲጎለብት አስፈላጊ የሆኑትን የሥራ አመራር ስልጠናዎች፣ ምርምሮችና የምክር አገልግሎቶች ፍላጎት ያጠናል፣*
2. *በተጠና ፍላጎት ላይ ተመስርቶ ለክልሉ የልማት ኃይሎች ከሥራ አመራር ጋር የተያያዙ የአጭርና የመካከለኛ ጊዜ ሥልጠናዎችን ይሰጣል፣*
3. *በተቋሙ የሚሰጡ የሥልጠና፣ የምርምርና የምክር አገልግሎቶች ምን ያህል ተጨባጭ ለውጥ ሊያመጡ እንደቻሉ ለማወቅ የሚያስችል ጥናት በየጊዜው ያካሂዳል፣*
4. *በሀገሪቱ በተለይም በክልሉ የሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት፣ ስልጠና፣ጥናትና ምርምር ተቋማት ጋር በመደጋገፍና በመቀናጀት ይሰራል፣*
5. *የስልጠናና የጥናት ፕሮጀክቶች በማዘጋጀት እንዲሁም የምክር አገልግሎቶችን በመስጠት ከተለያዩ ምንጮች ገቢ የሚያገኝበትን ሁኔታ ይፈጥራል፣*
6. *ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ተመጣጣኝ ክፍያ ሊያስከፍል ይችላል፣ ዝርዝር አፈጻጸሙ በክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የሚወሰን ሆኖ የሰበሰበውን ገቢም ለስልጠና፣ለምርምርና ለምክር አገልግሎቶች ማስፋፊያ ይጠቀማል፣ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ይከሳል፣ ይከሰሳል::*